ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ
Kinijit Ethiopian Cultural and Relief Organization in Toronto
998 Bloor St West,, P.O.Box 10666, Toronto, ON M6H - 1L8
Tel./ Fax: 416 - 516 1244




# ክቡራትና ክቡራን ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች

በክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ፕሬዚደንት የሚመራ የልዑካን ቡድን፣ ይፋ የስራ ጉብኝት ለማድረግ ወደ ካናዳ፣ ቶሮንቶ የሚመጣ መሆኑን በቅድሚያ እናሳውቃለን።

## *የልዑካን ቡድኑ የስራ ጉብኝት ዋናው ዓላማ፤*

1. በኢትዮጵያ የግንቦት 1997 ዓ/ም ምርጫን ተከትሎ፤ የወያኔ/ኢህአዲግ አስተዳደር፣ በንፁሃን ዜጎች ላይ የፈፀመውን ኢሰብዓዊ ድርጊት በመቃወም፤ የካናዳና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከህዝባችን ጎን እንዲቆም፤ እንዲሁም በግፍ የታሰሩትን የህዝብ እንደራሴዎች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን፣ የነፃው ፕሬስ አባላትን፣ የሲቪክ ማህበራት ተጠሪዎችንና የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን፤ ከእስር ለማስፈታት፤ በቶሮንቶና በመላው ካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ላደረጉት ሁለገብ ትግልና ድጋፍ ምስጋና ለማቅረብ፤
2. ወቅታዊውን የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና የሃገሪቱን የወደፊት ትልም አስመልክቶ ገለፃ ማድረግና ከህዝብ ጋር በመወያየቱ ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

ለልዑካን ቡድኑ ሊደረግ የታቀደውን የአቀባበል ስነስርዓትና ስብሰባው የሚካሄድበትን ቀንና ቦታ አስመልክቶ፤ ወደፊት ተከታታይ መግለጫ የሚወጣ መሆኑን እየገለጽን፤ በዚሁ የምስጋናና ልዩ የውይይት መድረክ እንዲሁም በታቀደው የአቀባበል ስነስርዓት ላይ፤ ለመገኘት እንድትዘጋጁ፤ እውነተኛውና አንጋፋው የቶሮንቶ ቅንጅት፤ የኢትዮጵያ የባህልና የእርዳታ ድርጅት፤ በካናዳ የድጋፍና የድርጅቶች አስተባባሪ ጽ/ቤት ጥሪውን ያቀርባል።

ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፤ በመላው ኢትዮጵያ፣ ግንቦት 2005 ዓ/ም ለተካሄደው ምርጫ ቅድመ ዝግጅት፤ እ.አ.አ. ጁላይ 11 ቀን 2004 ዓ/ም በቶሮንቶ ከተማ፤ ጽ/ቤታችን ባመቻቸው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ለኢትዮጵያውያን ባደረጉት ንግግር፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በማንቀሳቀስ በምርጫው ማሸነፍ እንደሚቻል ቃል መግባታቸው ይታወሳል።

የቶሮንቶ ቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ግብረኃይል፤ ሕዳር 2000 ዓ/ም